# የዛሬይቱ ኢትዮጵያና ስደተኛው ትውልድ

ከተሰማ ለማ -ሱዊዘርላንድ

መቻቻል 2ኛ ዓመት ቁ.1 (ጥር Jan.2000)

«የዛሬይቱ» የሚለው ቃል በቁሙ ካልተወሰደ በስተቀር ትናንትንና ነገን ጨምሮ ያመለክታል።ስለ ዛሬይቱ ኢትዮጵያ በምንነጋገርበት ጊዜ ስለ አለፈው የረዥም ዘመናት ታሪኳ ማሰላሰላችንናዛሬ ከምትገኝበት ገሀድ ሁናቴ ደግሞ ነገ ወይም ወደፊት ወዴት ልታመራ እንደምትችልመገመታችን ወይም ማሰባችን አይቀርም።

የሐገራችን ዘመናዊ ታሪክ የሚጀምረው ከ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ማለትም በዘመነ-መሣፍንት ማብቂያላይ የተነሱት ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ አንድነትና ዳር ድንበር መከበር፤ እንዲሁምለሕዝቧ ዕድገትና ብልፅግና ካደረጉት ብርቱ ጥረት ጋር ተያይዞ እንደሆነ ይታወቃል። «የዛሬዩቱኢትዮጵያ» የሚለው ፅንሠ-ሃሣብ የመነጨው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።የዚች አጭር መጣጥፍ ዓላማ ስለ ጥንታዊውና ማዕከላዊው ወይም ዘመናዊው የኢትዮጵያ ታሪክለማውሣት የታቀደ አይደለም። ይልቁንም ከዘመናዊው ታሪካችን ውስጥ እንኳ የአንድትውልድን ጊዜ ብቻ ቀንጭቦ አንዳንድ ነጥቦችን በማንሣት ከአንባቢያን ጋር የሃሣብልውውጥ ለማድረግ የተወጠነ ነው።

አንድ ትውልድ ሠላሣ ዓመት ነው። ይህም ማለት አንድ ሰው ተወልዶ፤ አድጎና ትዳርመሥርቶ ልጅ በማፍራት ለወግ ማዕረግ የሚበቃበት የዕድሜ ክልል ነው። ከዛሬ ሠላሣ ዓመትወዲህ በአገራችን ስለተከናወኑ አበይት የፖለቲካ፤ የኤኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳዮች በየመስኩበተሰማሩ የተለያዩ በሣል ምሁራን ሰፋፊ ትንታኔዎች የተሰጠበት ከመሆኑም ባሻገር ዛሬበሕይወት ከምንገኘው መካከል ብዙዎቻችን ሁናቴውን በቅርብ የተከታተልን የዓይን ምሥክሮችስለሆንን እዚህ ላይ ዝርዝር ነጥቦችን ማንሣቱ አስፈላጊ መስሎ አይታይም። እንዲያውበአጠቃላይ ግን በአለፈው የአንድ ትውልድ ዕድሜ ኢትዮጵያ በፈላጭ ቆራጭ አምባገነኖችአገዛዝ ተጠፍራ በማንኛውም ዓይነት መሥፈርት አንዲት ስንዝር እንኳ ዕድገት ሣታሣይ ዓመትከዓመት ትዕንግርታዊ ዝቅጠት ውስጥ ስትዘፈቅ እየተመለከትን ነው። ሕግ የሚባለው ነገርእንኳንስ ትርጉሙ ቃሉም ከሐገራችን ጠፍቶ ዛሬ ኢትዮጵያ በሰብዓዊ መብቶች ረገጣ «ስመ-ጥርና ታላላቅ» ከሚባሉ መንግሥታት መካከል ተፈርጃ ትገኛለች። በየዕለቱ ከቤቱ እየወጣ ደሙ«ደመ-ከልብ» በመሆን ሣይመለስ የቀረውን ዜጋ ብዛት ቤቱ ይቁጠረውና እንደ ጉጂኢንዱስትሪ በየመንደሩ በተስፋፉት እሥር ቤቶች ውስጥ ተጨናንቆ የሚገኘው የጎሊና እስረኛብዛት ያደባባይ ምስጢር ሆኖ ይገኛል። በረሃብ ሐገራችን በቅርቡ የዓለምን ክብረ-ወሰንእንደምትጨብጥ ተስፋ ተጥሎባታል። በንጉሠ-ነገሥቱ ዘመነ-መንግሥት በመቶዎች ይገመት የነበረውየስደተኛ ብዛት በአለፉት ሠላሣ ዓመታት ውስጥ በአስደንጋጭ ሁናቴ በመናር በሚሊዮን ሊቆጠር በቅቷል።

በተጠቀሰው የአንድ ትውልድ ጊዜ ውስጥ በሐገራችን ተከታትለው የነገሡት የደርግና የወያኔአምባገነን ገዢዎች በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ታሪክ አቻ የማይገኝላቸው አረመኔዎች መሆናቸውአጠያያቂ አይደለም። ደርግና ወያኔ ምናልባት በቅርፅ ይለያዩ እንጂ በአስተዳዳራዊ ይዘት ሁለቱምየለየላቸው አምባገነኖች ናቸው! ብቻ ወያኔን ትንሽ «ለዘብ» የሚያደርገው ሥልት ቢኖር ሰውበገደለ ቁጥር እንደ ደርግ «የፍየል ወጠጤ» እያለ አይሸልልም። በዚህ ረገድ የወያኔ «ሙያ-በልብ» ነው። በጕሣ ፖለቲካ ጦስ በአርባ ጉጉ፤

ወተር፣ በደኖ፣ ጂማ፣ ጉጂ፣ ጌዲኦ፣ ... ብዙሐንተጨፍጭፊው ሲያልቁ ወያኔ ድምፅ አሰምቶ አልፎከረም። ህልቀ መሣፍርት የኢትዮጵያ የሐገርመከላከያ ኃይል፣ የፖሊስ ሠራዊት፣ የደህንነትና የኢሠፓ አባላት እንዲሁም በርካታ በሣልምሁራንንና ሠራተኞችን በጅምላ አውላላ ሜዳ ላይ አውጥቶ ሲበትን ምንም ዓይነት ቀረርቶአላሰማም። ከእነዚህ እንደ አሮጌ ዕቃ ያለምንም ሕጋዊ ፍርድ ከተጣሉት ዜጎች ጋር በቀጥታበተያያዘ (በተሣሰረ) ሁናቴ ይኖሩ የነበሩ ኢትዮጵያውን በስንት ሚሊዮን ይቆጠሩ ይሆን? በሐገራችን በተደጋጋሚ የተከሰተው የድርቅ አደጋ ዛሬም በማንዣበብ ሕዝቡ ለከፍተኛ የረሃብ እልቂትተጋልጦ እያለ የወያኔ ሹማምንት ችግሩን በጸጥታ ከመመልከታቸውም በላይ እንዲያውም ኢትዮጵያ የተትረፈረፈየምግብ እህል ወደ ውጪ መላክ እንደምትችል በድፍረት ይናገራሉ። በሌላ በኩል፣ በአሁኑ ወቅትበየምክንያቱ ከወላጅ ቁጥጥር ውጪ በመሆን ወይም ራሣቸውን ከሥራ ገበታቸው በግፍየተባረሩ ወላጆቻቸውን ለመርዳት ብለው በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወጣቶች ቀድሞ ኅብረተ-ሰቡእንደ ነውር (ቊሮጕቅቅ) በሚቆጥራቸው ተግባራት ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ። ይህ ደግሞወጣቱን ወደ ወንጀል ከመገፋፋቱም በላይ እንደ ኤይድስ ለመሣሰሉ ቀሣፊ በሽታዎች ያጋልጣል።ተልዕኮው በከፊልም ቢሆን የተሣካለት ወያኔ እነዚህን የመሣሰሉትን አሰቃቂ ኢሰብአዊወንጀሎች (crime against humanity) በመፈፀም ላይ የሚገኘው ፋከራና ግርግር ሣያሰማነው። እነ ወዲ ዜናዊ ሕዝብን ድምፅ በሌለው መሣሪያ እያመነመኑ የሚፈጁት ከበሮ እየደለቁአይደለም! ፀጥ ብለው፣ ፀጥ አሰኝተው እንጂ።

እንግዲህ ስለ ሥደተኛው ትውልድ በምንነጋገርበት ጊዜም ከዚህ በላይ ከሞላ ጎደልከተዳሰሰው የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁናቴ ጋር በብዙ መልኩ የተያያዘ ሆኖ ይገኛል።

ለስደት የሚዳርጉ የተለያዩ አስከፊ ሁኔታዎች ይኖራሉ። ከነዚህም መካከል የተፈጥሮአደጋ፣ የዓየር መዛባት፣ ጦርነትና እነዚህን ተከትሎ የሚከሰተው ረሃብ፣ ድህነት፣... ወዘተ. ሰዎችአካባቢያቸውን እየለቀቁ እንዲሰደዱ ያስገድዳል። በሌላ በኩል አምባገነናዊ አሥተዳደርብልሹነት በተገዢው ሕዝብ ላይ የሚያሣድረው የተለያየ የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚና የማኅበራዊጉዳዮች መድልኦ፣ ጭቆናና ጭፍጨፋ ለስደት ምክንያት ይሆናሉ። የኢትዮጵያ ስደተኞች ጥያቄምበእነዚህ አበይት አሉታዊ ክስተቶች ውስጥ የሚካተት ቢሆንም፣ በተለይ በርዕሱ የተጠቀሰውትውልድ ጉዳይ ግን በአብዛኛው ከአሥተዳደር ብልሹነት የመነጨ ስለመሆኑ ከሠላሣ ዓመትወዲህ ያለው የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ ታሪክ ይመሰክራል። በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ለነበረውስቃይና ሰቆቃ በይበልጥ ተጋልጦ መከራ የበዛበት የአገራችን ወጣት ትውልድ መሆኑ ግልፅ ነው።ወጣቱ ከማናቸውም ዜጋ ይበልጥ በቀጥታ የደርግ፣ የሻዐቢያና የወያኔ አረመኔያዊ ጭፍጨፋናየእርስ በእርስ ጦርነት ሰለባ መሆኑ አይካድም። ከዚያ ሁሉ የተረፈው ደግሞ ሞራሉ ክፉኛተነክቷል፣ ጉልበቱ ላሽቋል፣ የሥነ-ልቦና ጽንአቱ ባክኗል። በአጠቃላይ የኅብረተ-ሰቡ የጀርባአጥንት፣ የሐገሪቱ የመከላከያ አለኝታ ሊሆን የሚችለው የዛሬው ወጣት ትውልድ ከቀደምትወላጆቹ የተረከበውን ታሪካዊ ኃላፊነት በሥርዓት እንዳይወጣ በተከታታይ የተነሱብንአምባገነኖች በገዛ ሐገሩ እያዋከቡ አደብ እንደነሱት መገንዘብ አያዳግትም። ታዲያ ይኸትውልድ ቢሰደድ ምን ይፈረድበታል?

እዚህ ላይ ስለ ዛሬዪቱ ኢትዮጵያዊ ወጣት ስደተኛ ስንነጋገር አንድ ሊታለፍየማይገባው ታሪካዊ ሐቅ ማንሣት ተገቢ ይሆናል። የዛሬ ሠላሣ ዓመት ግድም በሐገራችንበነበረው ሥርዓት ላይ የለውጥ አመፅና አብዮት በግብታዊነት ከየአግጣጫው በተሟሟቀበትወቅት የዛሬው ወጣት ትውልድ ከፊሉ በእናቱ ማህፀን፣ ከፊሉ ደግሞ ጥና ቢል የአራትናየአምስት ዓመት ሕፃን ልጅ ነበር። በ66ቱ አብዮት ዋዜማ ወጣት የነበረው ደግሞ ዛሬ በስደትምይሁን

አገር ቤት በጎልማሣነትና በአዛውንትነት የዕድሜ ክልል ውስጥ በሕይወት የምንገኘው«ታሪከኞች» ነን። ከዛሬዎቹ በወጣትነት የዕድሜ ክልል ውስጥ ከሚገኙት ኢትዮጵያውያንመካከል በዚያን ጊዜ አንዳቸውም እንኳ ለውጥ! ለውጥ! አብዮት! አብዮት! ብለው የተቃውሞሠልፍ አልወጡም፤ ድንጋይ አልወረወሩም፤ ከፖሊስ ጋር አልተጋጩም። በአጭሩ የዛሬዎቹኢትዮጵያውያን ወጣቶች ያኔ ሁሉም ገና ጨቅላ ሕፃናት ስለነበሩ ለውጥ፤ አብዮት በማለት«ረብሻ አልፈጠሩም» የተባለው አብዮት ፈንድቶ ውሎ ሲያድር ግን ጦሱ፤ አበሣውና መከራውበእነሱ ላይ በረከተ! «አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ» እንዳይባል፤ ምንም ይሁን ምን የሐገር ጉዳይነውና የአባት ዕዳ ለልጅ ተረፈ። ይህንንም ዕዳ ወጣቱ ትውልድ ከፍተኛ መስዋዕትነት እየከፈለእስከ ዛሬ ድረስ በመቀፍቀፍ ላይ ይገኛል። በሌላ በኩል፤ በደርግም ሆነ በወያኔ አገዛዝ በግልፅእንደታየው ያገር ቤቱ አበሣና ፍዳ አቅም ከሚችለው በላይ ስለበዛበት አብዛኛው ወጣት አገርለቅቆ ለመሰደድ ተገደደ። ይህ ሐቅ በግልፅ መታወቅ ይኖርበታል።

የስደት ኑሮ ለአብዛኛው አገር ቤት ሆነን ካሰብነው በላይ በጣም የከበደና አስቸጋሪእንደሆነ የደረሰበት ይመሰክራል። እርግጥ አንዳንድ ወጣቶች አገር ቤት ችግር ሣይገጥማቸውወደ ውጪ ሐገር፤ በተለይም ወደ አውሮጳና አሜሪካ መውጣትን በልጅነት መንፈስ እንደ ፋሽንበመውሰድ ወላጆቻቸውን እያስቸገሩ ወጥተው እራሣቸውን ለችግር የዳረጉ ስደተኞች አሉ።እንደ እነዚህ ያሉ ወጣቶች ካላፈሩ በስተቀር አሁኑኑ ወደ አገር ቤት ቢመለሱ ይመረጣል።በምዕራቡ ዓለም ስደተኛ ሆኖ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም (ኮሌጅ፤ ዩኒቨርሲቲ፤...) ነፃ የትምህርትዕድል (scholarship) የማግኘቱ ሁናቴ እጅግ የጠበበ ነው። ምዕራባውያን ሐገሮች እራሣቸውበሥራ አጥነት ችግር ተወጥረው ስለሚገኙ በሙያውና በችሎታው ተወዳድሮ ሥራ የሚያገኝስደተኛ ቢኖር ምናልባት ከሺህ አንድ ቢሆን ነው። ስለሆነም አብዛኛው ባለዲፕሎምና ባለዲግሪ ስደተኛ ኑሮውን የሚገፋው የተቀባዩ ሐገር ዜጎች በብዛት በማይቀጠሩበት (በማይፈልጉት) የጉልበት ሥራ ላይ በመሠማራት ነው። ይህንንም የሚያገኘው «ዕድለኛ» ስለሚሆን የተቀረውስደተኛ ከመንግሥት የምትሰጠውን የሕይወት ማቆያ ዳረጎት እየተቀበለ፤ ይህ በማይደረግበትሐገር ደግሞ የሰብዓዊ ዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶችን እጅ እያየ ነው የሚኖረው። በዚህ ላይ የሐገር፤የወገን፤ የዘመድ አዝማድ ናፍቆት አለ! ስለዚህ ለከፍተኛ ችግር የተጋለጡ ወጣቶችመጀመሪያውኑ ከሐገር ባይወጡ፤ ከወጡም በኋላ ሁኔታውን እንዳዩት ወዲያውኑ እንዲመለሱ ይመከራል።አብዛኛው ስደተኛ ግን በአንድ ምክንያት ይሁን በሌላ፤ የአስተዳደር ብልሹነት ሰለባ በመሆኑ በአሁኑወቅት ወደ አገር ቤት ለመመለስ እጅግ ያስቸግረዋል።

ስደት ጠንክረው በአግባቡ ከሠሩበት እራሱን የቻለ የትግል ስልትና መድረክ እንደሆነ የታወቀነው። ስደተኛ ድርጅቶችም ሆኑ ግለ-ሰቦች፤ ውጪ ሐገር፤ በተለይም በምዕራባውያን ሐገሮችውስጥ ከሞላ ጎደል ዛሬ እኛ ሐገር ከሚታየው በላቀ ነፃነት መንቀሣቀስ ይችላሉ። የእያንዳንዱተቀባይ ሐገር ሕግና ደንብ በሚፈቅደው መሠረት ስብሰባዎችንና የተቃውሞ ሰልፎችንማካሄድ፤ ዓላማንና ፕሮግራምን ማስተዋወቅ፤ ዕርዳታ መሰብሰብ፤ ሌላም፤ ሌላም የወያኔንመንግሥት የሚያጋልጡ እንቅስቃሴዎችን ማከናወን ይቻላል።

ለኢትዮጵያ አበይት ችግር ዋና መፍትሄ የሚገኘው ከኢትዮጵያውያን ዘንድ መሆኑአጠያያቂ ባይሆን፤ የውጪ ኃይሎች (external factors) ሊጫወቱ የሚችሉት አዎንታዊወይም አሉታዊ ሚና ደግሞ የሚናቅ አይደለም። ሻዐቢያና ወያኔ ደርግን አቸንፈው ለሥልጣንየበቁት በኢትዮጵያ ሕዝብ ድጋፍና ፍላጎት ላይ ብቻ ተመሥርተው ነበር? የደርግና የወያኔየሥልጣን ርክክብስ በዋሽንግተንና በሌሎች መዲናዎች ሲቦካ ከርሞ በመጨረሻ የተጋገረውለንደን አልነበረም? በውጭ፤ በተለይም በጎረቤት ሐገሮች ከፍተኛ

የፖለቲካ ወይም የመስተዳድርለውጥ ሲከሰት ኢትዮጵያውያን ትኩረት እንሰጣለን? በአጠቃላይ የውጭውን ሁናቴያላገናዘበ የውስጥ የፖለቲካ ትልም ውጤታማነቱ አጠያያቂ እንደሚሆን ግልፅ ነው።

በውጭ ሐገር የሚገኙ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችም ከዚህ በላይ እንደተጠቀመው፤ካሉበት ሁናቴ አመቺነት አኳያ በርካታ ተግባራትን ማከናወን ይችላሉ። የምዕራባውያን ሐገሮችመሪዎች እንደ እኛ ሐገር አምባገነኖች ሕዝብን አይንቁም። ይልቁንም ሕዝቡን ያዳምጣሉ።ስለሆነም በስደት የሚገኙ ድርጅቶች በያሉበት ኅብረተ-ሰብ ውስጥ በትጋት በመንቀሣቀስ ስለወያኔ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ፣ ስለጐሣ ፖለቲካ ጠንቀኛነት፣ ወያኔና ሻዐቢያ ስለሚያካሂዱትጦርነት አደገኛነት፣ በሐገራችን ስለሚታየው የረሃብ አደጋና የኤድስ ወረርሽኝ፣ ወህኒ ቤትስለሚማቅቁት፣ እንደወጡ ስለሚቀሩት፣ በግፍ ስለሚገደሉት ወገኖቻችን፣ ስለ ምርጫ ተብዬው፣... ወዘተ. በተለያየ መንገድ ሣይታክቱ ለሕዝብ በማስረዳት በርካታ ድጋፍ ማሰባሰብ ይቻላል።በተጨማሪም የፓርላማ አባላትን፣ የመንግሥት ባለሥልጣናትን፣ ሥሙ-ጥር ግለሰ-ቦችን፣ጋዜጠኞችን፣ የኪነት ባለሙያዎችን፣ ወዘተ. በየግል እየቀረቡ ወዳጅነታቸውን በማፍራት በወያኔላይ ተፅዕኖ የሚያሣድሩ ብዙ ቁም ነገሮችን ማከናወን ይቻላል። እንዲሁም በጠንካራአስተባባሪዎችና የድጋፍ ሰጪ ኮሚቴዎች ዙሪያ እያንዳንዱ ስደተኛ በዳረጎትም ይሁን ለፍቶከሚያገኘው በየወሩ ለአንዲት ፊንጃል ቡና የሚከፍላትን ሂሣብ ብቻ እንኳ ለሐገር ጉዳይቢያወጣ ከየአካባቢው የሚሰበሰበው ገንዘብ ቀላል እንዳልሆነ መገመት አያዳግትም። እዚህ ላይ«ወርቅ የተጫነች አህያ የማታፈርሰው ምሽግ የላትም» የሚለውን ያበው ብሒል በደንብያጤኗል።

ለማጠቃለል ያህል፣ ከሠላሣ ዓመት ወዲህ ያለችው የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ ባሁኑ ወቅትከምን ጊዜውም ይበልጥ አሣሣቢ ሁናቴ ላይ እንደምትገኝ ግልፅ ነው። በመሆኑም ዛሬከምትገኝበት ተጨባጭ ሁናቴ በመነሣት የነገው አግጣጫዋ ኢትዮጵያውያንን በሙሉ ያሰባስባል። ወያኔናተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎች ያለምንም ዴሞክራሲያዊ መፍትሄ ተፋጥጠው ይገኛሉ። የወያኔው መሪ መለስዜናዊ ካሁን ቀደም ካንዴም ሁለት ሦስቴ ከተቃዋሚ ወገኖች የቀረበላቸውን ሠላማዊየድርድር ጥሪ በንቀት እንዳጣጣሉት ሁሉ፣ ዛሬም «ጠንካራ ተቃዋሚ ፓርቲ የለም» የሚለውንየፌዝ መፈክራቸውን አንግበው ይገኛሉ። እንዲያውም በቅርቡ ሊደረግ የታቀደው ምርጫተብዬ ቴአትር የተለመደውን «ተጨፈኑ ላሞኛችሁ» ቀልዳቸውን ለማሣየት በመዘጋጀት ላይናቸው። በአንፃሩ በአሥተዳደር ብልሹነት፣ በጦርነትና በረሃብ የተነሣ ሐገር እየለቀቀየሚኮበልለው ስደተኛ ቁጥር ዕለት በዕለት እየጨመረ ሊቀጥል ይችላል። በአጠቃላይ ከወያኔ ጋርበሠላማዊና በዴሞክራሲያዊ የትግል ስልት የመደራደሩ ተስፋ ባሁኑ ወቅት ተሟጥጦ ያለቀበትጉዳይ ይመስላል። ካለው ተጨባጭ ሁናቴ ለመገንዘብ እንደሚቻለው ከእንግዲህ ወዲያ የወያኔመሪዎች እንደ ማንኛውም አምባገነን በኃይል ተገደውና ተዋርደው ካልሆነ በስተቀርበዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና በፈቃደኝነት ከሥልጣን አይወርዱም! መፍትሄውም ትግልና ትግልብቻ ይሆናል! ወያኔን በኃይል አሽቀንጥሮ ለማውረድ ከተለያዩ አግጣጫ በተለያየ መልኩየሚከናወን የተቀነባበረ ትግል! ሌላ አማራጭ አይታይም።

በዚህ ረገድ በውጭ ሐገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች በሙሉ ከምንጊዜውም ይበልጥየተሰደዱበትን ምክንያት በሚገባ በማጤንና ለስደት በዳረጋቸው አስከፊ አገዛዝ ላይም በየዕለቱይበልጥ በመቆጨት በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ አቅም የፈቀደውን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማከናወንይጠበቅባቸዋል። የወቅቱ ብሔራዊ ኃላፊነትና ግዴታም ነው። ሐገር ቤትም ሆነ በስደት፣ በፖለቲካምይሁን በትጥቅ፣ በማንኛውም አካባቢና ሥልት ወያኔን ከሥልጣን ለማስወገድ በሚደረገውትግል በድርጅት ሥር መሰባሰቡ ወሣኝ እንደሚሆን ብዙ

ጊዜ ተደጋግሞ ተገልጿል። በዚህበኩል ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች (ነባር ኅብረ-ብሔር ፓርቲዎችም ጭምር)፤ በ«ኢተፓድኅ» ጥላሥር በመሰባሰብና በጋራ በሚያግባቡዋቸው ዓበይት የሐገራችን ጉዳዮች ላይ በመስማማትበኅብረት መሥራት ከጀመሩ ዓመታት እየተቆጠሩ ነው። በትጥቅ ትግሉም በኩል «ኢአግ-ኢአሠ»በአንዳንድ የሐገራችን ክልሎች ውስጥ ፀረ-ወያኔ የሽምቅ ውጊያ በማካሄድ ላይ እንደሚገኝከተሰማ ሰንብቷል። የ»ኢተፓድኅ» እንዲሁም የ«ኢአግ-ኢአሠ» እንቅስቃሴ ገና ከጅምሩእንደሚታየው በዓይነቱም ሆነ በይዘቱ ተስፋ የሚጣልበት የትግል ቅንጅት ይመስላል። ሌሎችምተቃዋሚ ኃይሎች «ድር ቢያብር አንበሣ ያስር» ነውና በሂደት ሊፈቱ የሚችሉ ጥቃቅንልዩነቶችን በመቻቻል በዚሁ የትግል ሥልት ዙሪያ ቢሰባሰቡ በቅርብ ጊዜ ውስጥ አመርቂ ውጤትእንደሚገኝ አያጠራጥርም።

በመጨረሻም፤ በአሁኑ ወቅት ለማንኛውም ለሐገሩ ነፃነት ቀንዐዊ ለሆነ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በያለበት አካባቢ በትግል መብቱንና ክብሩን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ መድረኮች አልታጡም።ቁም ነገሩ አቅምና ችሎታ በፈቀደው መጠን በተለያየ መንገድ ትግሉ ውስጥ ገብቶ በመሣተፉ አስተዋፅዖ ማበርከት ነው። በተረፈ ዳር ቆሞ «የሚረባ ተቃዋሚ ድርጅት የለም» ማለቱ የኋላ ኋላ ታላቅ ትዝብት ላይ የሚጥልና ለሕሊና ጸጸት የሚዳርግ ዕርባና ቢስ ትችት ይሆናል። በዴሞክራሲያዊ ባሕል እያንዳንዱ ዜጋ በሐገሩ ጉዳይ በግልፅ የመሰለውን አቋም የመውሰድ መብቱ የተከበረ ነው። በዛሬዪቱ ኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁናቴም ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወያኔን ወይም በአሁኑ ወቅት የሚንቀሣቀሱ ተቃዋሚዎችን እንደ የአመለካከቱ የመደገፍና የመቃወም መብቱ የተጠበቀ ነው። ነገር ግን ምንም ዓይነት አማራጭ ሣያቀርቡ ወያኔንም ተቃዋሚንም ዳር ቆሞ ማማት አደገኛ አቋም ይሆናል፤ ፍርሃትንና አድር-ባይነትን ለማባበል የሚተረብ ባዶ አሉባልታ! **በቃ**!